# ስንቱን እንታገል?

ሺዎችን የበላ ፣ ሺውን የሰለበ
የደርግን ቡችላ ፣ በደም የታጠበ
በደሃ ደም አብጦ ፣ ጫንቃው የደለበ
ወይንስ ዘረኛውን ፣ በጎጥ የጠበበ
ስንቱን እንታገል ፣ ስንቱ አኮበኮበ ፣፣

ስንቱን እንታገል ፣ ስንቱን እንጣራ
አንጃ ግራንጃውን ፣ አቋሙ ያልጠራ
ለባዕድ ያደረ ፣ በሆዱ የሚሰራ
ኮሽ ባለ ቁጥር ፣ የሚሸሽ ደንባራ
ስንቱን እንታገል ፣ ስንት አለ ጸርጻራ ፣፣

ሕዝባዊ ነኝ ብሎ ፣ ሄዶ የተለጠፈ
ከጅ አይሻል ዶማ ፣ ወያኔን ያቀፈ
ባቋሙ ያልጸና ፣ ቃሉ የታጠፈ
ቢያጥቡት የማይጠራ ፣ ጨቅይቶ ያደፈ
ስንት ጀግና አስበላ ፣ ስንቱን ተቀጠፈ
ስንቱን ስንታዘብ ፣ ስንት ዘመን አለፈ
ስንቱን ስንታገል ፣ ስንቱ ተጠለፈ ፣፣

ድርጅት አፍርሶ ፣ ድርጅት ፈጣሪ
ወላዋይ ልበ ሙቅ ፣ ወሬ ቀባጣሪ
አይን ሲያፈጡበት ፣ የሚያረጥብ ሱሪ
የጅ አዙር ወያኔ ፣ የመልስ ተጠሪ
ስንቱን እንታገል ፣ ስንት አለ መሰሪ ፣፣

ዞር ሲሉ አንጃ ፣ ዞር ሲሉ ጎጠኛ
የትላንቱ ፈሪ ፣ የዛሬው አርበኛ
የታራራው አምበል ፣ የምላስ ጦረኛ
ያርባመቱ ታጋይ ፣ የዛሬው ምንደኛ
አንድ እግሩ መቃብር ፣ የገባ ተረኛ
ቂጢኛም አፍቅሮ ፣ የሆነ ሴሰኛ
ሲያልቅ አያምር አሉ ፣ ስንቱን አየን እኛ
ስንቱን እንታገል ፣ ስንት አለ ቅጥረኛ ፣፣

አገር ያፈረሰ ፣ የገደለው ሌላ
የሚያውደለድልው ፣ ፍርፋሪ የበላ
ወያኔን ልታገል ፣ ወይ የሱን ዲቃላ
የትግል ደንቃራ ፣ ምላሱ የሰላ
ስንቱን እንታገል ፣ ስንት አለ ደላላ ፣፣

በሕዝብ ትግል ላይ ፣ እንገቱን ያዞረ
ሀሰትን አንግሶ ፣ ሃቅን የቀበረ
አገሩን የሸጠ ፣ ለሆዱ ያደረ
ምን ትውልድ ላይ ፣ ደረስን ምኑ ተፈጠረ
አንጃም አይን አወጣ ፣ ዘመን ተቀየረ
ከትላንቱ ዛሬ ፣ ትግላችን መረረ
ስንቱን እንታገል ፣ ስንቱ ተቀጠረ ።

ታዛቢው